በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር
Ref. No የህ/ም/ማጠ/ዳ/5477/13
ቀን
Date 25/12/2018 ዓ.ም

ለአማራ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 313/2018 ዓ.ም ላይ እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት ቢሮው በቁጥር ን/ዘ/ም/100/867/18 በቀን 18/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 03/2010 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 03/2010 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 167/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲወል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 10 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

'ከሰላምታ ጋር'

የህግ ም/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ//
- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793 ✉ 995 Fax- 0582221530
☎ 058 220 37 57

መመሪያ ቁጥር 167/2018 ዓ.ም

የአማራ ክልል የነዳጅ አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ

የሰው ልጅ ለኃይል ምንጭነት ከሚገለገልባቸው የኢንዱስትሪ ውጤቶች መካከል አንዱ ነዳጅ ሲሆን ለኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎት የሚጫወተው ሚናና የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ፤

ምርቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከአለም ገበያ እየተገዛ የሚቀርብ በመሆኑ የመሸጫ ዋጋውና የስርጭት ስርዓቱ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በአግባቡ ተደራሽ ለማድረግ የህግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊና ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳዩ በመሆኑ፤

የአማራ ክልል ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 230/2008 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ክልል የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1672018 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

1/ "ነዳጅ" ማለት ድፍድፍ ነዳጅና ከድፍድፍ ነዳጅ፣ ከከሰል ድንጋይ፣ ከሸስት፣ ከቅርፊት፣ ከፒት የሚሰራ ማንኛውም ፈሳሽ/ ጋዝ ነው፤

2/ "የነዳጅ ውጤት" የተፈጥሮ ድፍድፍ ነዳጅን ባዮፊውልን ወይም ሴንቴቲክ ነዳጅን ከማጣራት ወይም ከማቀነባበር የተገኘ ማለት ነው፤

3/ "የነዳጅ አቅርቦት ስራ" ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ሃገር ውስጥ የማስገባት፣ ወደ ውጭ የመላክ፣ የማጣራት፣ የማደባለቅ፣ የማጓጓዝ፣ የማከማቸት፣ የማከፋፈል፣ የመቸርቸር ወይም ከእነዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ማንኛውም ስራን ያካትታል፤

4/ "የአቅርቦት ሰንሰለት" ከነዳጅ አቅርቦት ስራ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ተግባራት ፣ ተቋማትና መሳሪያያዎችን ያካትታል፤

5/ "የነዳጅ ተቋም" ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ለማጣራት፣ ለማደባለቅ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ ወደ ውጭ ለመላክ፣ ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማከፋፈል፣ ለመቸርቸር ወዘተ ተግባር ላይ የተሰማራ ማንኛውም ተቋም ማለት ነው፤

6/ "ማጣሪያ" ከድፍድፍ ነዳጅ የነዳጅ ምርቶችንና ፈሳሽ ፔትሮሊየም ጋዝ ለማምረት የሚያገለግ ልማጣሪያ ፋብሪካ ነው፤

7/ "ግንባታ" ማለት የነዳጅ ተቋም ግንባታ ማለት ነው፤

8/ "ሸማች" ማለት ለማምረት ስራ ወይም መልሶ ለመሸጥ ሳይሆን ዋጋውን ራሱ ውይም ሌላ ሰው የሚከፍልለት ሆኖ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ ፍጆታ የሚሆን የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚገዛ የተፈጥሮ ሰው ነው፤

9/ "የሸማቾች ጥበቃ" ማለት ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚገዛው ህብረተሰብ መብት በህግ እንዲጠበቅና ተግባራዊ እንዲሆን የሚደረገውን የመንግሥት፣ የድርጅቶች/የማህበራት፣ የግለሰቦችና የንግዱ ማህበረሰብ ጥረትነው፤

10/ "መሠረታዊ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት" ማለት በገበያ ላይ እጥረት በመፈጠሩ ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ ሊያስከትል የሚችል ከሸማቾች የየዕለት ፍላጐት ጋር የተገናኘ የንግድ ዕቃ ወይም አገልግሎት ነው፤

11/ "ነጋዴ" ማለት የሙያ ሥራው አድርጎ ጥቅም ለማግኘት ሲል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የንግድ ሥራ ነው ተብሎ በሕግ የሚወሰነውን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤

12/ "መደ ባለቅ" ማለት የተሻለ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት ሲባል የነዳጅ ውጤትን ከባዮፊውል ከሌሎች የቴክኖሎጅ ውጤት ጋር በተወሰነና በተመጣጠነ መጠን የማቀላቀል ተግባር ነው፤

13/ "ብክለት" ማለት ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለውን የነዳጅ ውጤት ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ካለው የነዳጅ ውጤት ጋር በመደባለቅ የሚከሰት ሲሆን ለሰው፣ ለሌሎች ህይወት ላላቸው ነገሮች፣ ለአካባቢ፣ ለመሳሪያ ወይም ማሽነሪዎች አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፤

14/ "ማከማቸት" ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ወደ ሌላ ማከማቻ ወይም ማከፋፈያ እስኪሰራጭ ድረስ

ለተወሰነ ጊዜ ማቆየት ማለት ነው፤

15/ "ማከፋፈል" ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረግ ማለት ነው፤

16/ "ጅምላ ሻጭ" ማለት ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን ከአምራች/አስመጭ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ሲሆን አስመጭ/አምራቹ ቀጥታ ለቸርቻሪ ሲሸጥ እንደ ጅምላ ሻጭ ይቆጠራል፤

17/ "ነዳጅ ማደያ" ማለት ማንኛውንም ነዳጅና የነዳጅ ምርቶች በዘመናዊ ዘዴ በችርቻሮ ለተጠቃሚ ለመሸጥ የተቋቋመ ድርጅት ነዉ፤

18/ "የገበያ አረጋጊ ግብረ ሀይል" ማለት የመሰረታዊ ምርቶችን ዋጋና ስርጭት ለመቆጣጠር የኢፌዴሪ ንግድ ሚ/ር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2004 አንቀጽ 5መሰረተ በየደረጃው የተቋቋመ የገበያ አረጋጊ ግብረ ሀይል ነው፤

19/ "የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት" ማለት ለንግድ ዓላማ ቢሆንም ባይሆንም ነዳጅና የነዳጅ ዉጤቶችን የማጣራት፣ የመደባለቅ፣ ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ የመላክ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ፣ የመቸርቸር ብቃትን ለማረጋገጥ የተሰጠ የምስክር ወረቀት ነው፤

20/ "ክትትል" ማለት የነዳጅ ተቋማት በተሰጣቸው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረት መስራትና አለመስራታቸውን የማረጋገጥ ሂደት ነው፤

21/ "ባለፈቃድ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 838/2006 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /የግንባታ ፈቃድ/ የተሰጠው አካል ማለት ነው፤

22/ "አስተዳደራዊ ርምጃ" ማለት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የንግድ ድርጅት ማሸግ፣ የንግድ ድርጅት ማገድ ወይም የንግድ ሰራ ፈቃድ መሰረዝ የመሳሰሉ በንግድ ተቋም የሚወሰድ እርምጃ ማለትነው፤

23/ "ቢሮ" ማለት የአብክመ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ ማለት ነው።

3. <u>የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ተፈጻሚ ይሆናል።

4. <u>የመመርያው አላማ</u>

የዚህ መመርያ ዋና አላማ፣ ለክልሉ ህዝብ ከመንግስት የሚቀርቡትን የነዳጅ ምርቶች ፈጣን አቅርቦት፣ ፍትሃዊ ስርጭትና ተደራሽነት በማረጋጋጥ እንዲሁም ነዳጅን ከብክነት በማዳን የህብረተሰቡን እርካታ ማረጋገጥ ነው።

ክፍል ሁለት

የአስፈጻሚ ተቋማት ተግባርና ሃላፊነት

5. የክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

1/ በክልሉ ስር በሚገኙት የነዳጅ ተቋማት ላይ ስለ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የአካባቢ፣ ደህንነት፣ የቴክኒክ ሁኔታ፣ በነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ጥራት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ሥራ ያከናውናል፤

2/ ለነዳጅ ማደያዎችና ከማደያ ውጭ የችርቻሮ ንግድ ለሚሰሩግለሰቦችና ተቋማት በደንቡእና በመመሪያው መሰረት መስፈርቶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ይሰርዛል፣ ያግዳል፤

3/ የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ አፈጻጸምን አስመልክቶ በሚዘጋጁ መመሪያዎች ላይ ለፌድራል ተቋማት ግብዓት ይሰጣል፤

4/ በክልሉ የነዳጅ ስርጭት በፍትሀዊነት ለህብረተሰቡ መድረሱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

5/ ባለሀብቶች ወደ ነዳጅ አቅርቦት ኢንቨስትመንት እንዲገቡ ያበረታታል፣ በክልሉ ሁሉም ቦታዎች ኦፕሬሽናል ዴፖዎች በባለሀብቶች እንዲገነቡ ይደግፋል፣ያስተባብራል፤

6/ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የነዳጅ ማደያዎች በብዛት እንዲገነቡ ባለሀብቶችን ያስተባብራል፣ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

7/ እንደ ክልል የነዳጅ እጥረት ሲፈጠር ከክልሉ ስትራቴጅካል ዴፖዎች ነዳጅ እንዲቀዳ ከፌድራል ተቋማት ያስፈቅዳል፣ ያስፈጽማል፤

8/ በነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት ለአቅም ግምባታ ስራዎች ኘሮጀክቶች ሲፈቀዱ ለነዚህ ማስፈጸሚያ ለክልሉ የሚተላለፈውን በጀት በመንግስት የበጀት ህግና ደንብ መሰረት ለታለመለት ሥራ ያውላል፤

9/ ስለብቃት ማረጋገጥ፣ ክትትልና ቁጥጥር፣ እንዲሁም የነዳጅ ፍትሃዊ ስርጭት ሁኔታ በየወሩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለሚመለከተው የፌደራል ተቋም ያቀርባል፤

10/ የነዳጅ ማደያ የሌላቸዉ የወረዳ ዋና ከተሞችን የነዳጅ የችርቻሮ የመሸጫ የተመን ዋጋ ከንግድ ሚኒስቴር በተገለጸለት መሰረት የመወሰንና የማሳወቅ ሃላፊነትን ይወጣል፤

11/ በነዳጅ ሥርጭት አፈጻጸም መመሪያ መሰረት የነዳጅ ምርቶችን እስከ ሸማቹ ህብረተሰብ ሊደርስ የሚያስችል የስርጭት አፈጻጸም፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

12/ የነዳጅ የስርጭት መረጃና የአፈፃፀም ሪፖርት በጹከፍከታች ይቀበላል፣ ለፌድራል የማዕድን የተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ ሚኒስቴር፣ ለንግድ ሚኒስቴር ሪፖርት ይልካል፤

13/ በክልል የገበያ አረጋጊ ግብረ ኃይል ኮሚቴ ውስጥ በሰብሳቢነት ይሳተፋል፤ ተገቢውንም የስርጭት መረጃ ለግብረ-ኃይሉ በጹሁፍ ያቀርባል፤

14/ ከነዳጅ አቅራቢ ካምፓኒዎች እስከ ነዳጅ ማደያዎች ድረስ ያለውን የነዳጅ አቅርቦት ፍሰት መቆጣጠር የሚያስችል መረጃ መያዙን ያረጋግጣል ለዚህም ራሱን የቻለ የክትትልና ቁጥጥር ሥርአት ይዘረጋል፤

15/ በህዝብ ማስታወቂያ መሰረት የነዳጅ ሽያጭ መፈጸሙን፣ በተተመነው ዋጋ መሰረት የሚሸጥ መሆኑን የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

16/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የነዳጅ ማደያዎች የማሽን ልኬታ ትክክለኛነት በየጊዜው የቬሪፊኬሽን ምርመራ ስራ ያካሂዳል።

6. <u>የዞንና የሜትሮፖሊታንት ከተሞች ንግድ መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ በዞኑ ውስጥ ያሉትን የነዳጅ ማደያዎች የማሽን ልኬታ ትክክለኛነት በየጊዜው የቬሪፊኬሽን ምርመራ፤ የፊዚካል ኢንስፔክሽን ቁጥጥር ያካሂዳል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

2/ ነዳጅ ማደያዎች የነዳጅ መቀላቀልን ህገወጥ ድርጊት እንዳይፈጽሙ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

3/ ከወረዳው ዋና ከተማ ውጭ የሚገኙ የንዑስ ከተሞችን የነዳጅ ችርቻሮ ንግድ የሚያከናውኑትን አካላት የነዳጅ የችርቻሮ የመሸጫ ተመን ዋጋ በዞኑ የገበያ አረጋጊ ግብረ ሃይል ያስወስናል፣ ስራ ላይ ያውላል፤

4/ ለወረዳና ከተማ የንግድ ተቋም የስነ ልክ ባለሙያዎች የአቅም ግምባታ ስልጠና ይሰጣል፣ በመስክ ድጋፍ የተግባር ስልጠና ይሰጣል።

7. <u>የገጠር ወረዳና የከተማ አስተዳዳር ንግድ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1/ የነዳጅ ማደያዎች በተገቢው ጊዜና መጠን የነዳጅ ክምችት መያዛቸውንና ማሰራጨታቸውን ክትትል ያደርጋል፤

2/ ከነዳጅ ማደያዎች ወርሃዊ የነዳጅ ሽያጭ ሪፖርት ይሰበስባል፣ ለበላይ አካል በጽሁፍ ያሳዉቃል፤

3/ የነዳጅ ማደያዎችን ቢሮው ባዘጋጀው የመስክ ኢንስፔክሽን መቆጣጠሪያ ቅጽ መሰረት በየጊዜው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በድርጅቱ የአስተያየት ደብተር ላይ አስተያየት ይሰጣል፣ ከማደያው ወኪል ወይም ባለሀብትጋር ይፈራረማል፣ ችግር ሲኖር አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

4/ የነዳጅ ሪዘርቭን ይከታተላል፣ ሪዘርቭ ነዳጅን በኩፖን ለማደያ ትዕዛዝ በመስጠት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አካላት ነዳጅ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

5/ ህገወጥ የነዳጅ ንግድን፣ ዝዉዉርን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን ህግ የማስከበር ተግባር ይፈጽማል፤

6/ አዳዲስ የነዳጅ ማደያዎች ሲከፈቱ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማለትም ቦታው በግለሰቡ ስም ለነዳጅ ማደያ የተሰጠ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሳይት ፕላን፣ የአካበቢ ደህንነት ተጽእኖ ግምገማ (EIA) ሰርቲፊኬት፣ ግምባታው በዲዛይኑ መሰረት ተሰርቶ ስለመጠናቀቁ የሚያሳይ የመሃንዲስ ማረጋገጫ ደብዳቤ፣ ማደያው ለሶስቱም አይነት ነዳጆች የተገነባ ስለመሆኑ፣ እያንዳንዱ ታንከር ምን አይነት ነዳጅ፣ ስንት ሊትር እንደሚይዝ የሚገልጽ፣ የነዳጅ ማደያውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቅሜታና አስፈላጊነት የሚገልጽ የንግድ ሴክተር የድጋፍ ደብዳቤ፣ የነዳጅ አቅራቢ ካምፓኒና የነዳጅ ማደያ ወኪል (ዲለር) የስምምነት ውል፣ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት (በዞን ንግድና ገበያ ልማት መምርያ) የንግድ ሚኒስቴር ወይም የክልል ንግድ ቢሮ ፍቃድ ይሰጣቸው የሚል ህጋዊ ደብዳቤ፣ ከንግድ ሚኒስቴር የተላከ የነዳጅ ማደያ የችርቻሮ የዋጋተመን፣ ሌሎች በምዝገባና ፍቃድ አዋጅ 980/2008 የንግድ ስራ ፍቃድ ለመስጠት የተቀመጡ መስፈርቶች ሲቀርቡ ብቻ የነዳጅ ማደያ የንግድ ስራ ፍቃድ ይሰጣል፤

7/ እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ለነዳጅ ማደያው አስቀድሞ የንግድ ስራ ፈቃድ ሰጥቶ የተገኘ የምዝገባና ፈቃድ ባለሙያ ወይም ፈቃድ እንዲሰጠው ትዕዛዝ የሰጠ ቡድን መሪ ወይም ሃላፊ በዲስፕሊን ይጠየቃል።

ክፍል ሦስት

ስለ ነዳጅ ማደያዎች አሰራር

8. የነዳጅ ማደያ ግዴታዎች

ማንኛውም የነዳጅ ችርቻሮ ለመስራት ወደ ስራ የገባ ነዳጅ ማደያ፦

1/ በህዝብ ማስታወቂያ በተገለፀው የነዳጅ ዋጋ ተመን መሰረት ነዳጅ ሪዘርቭ ካልገባ በስተቀር የነዳጅ ምርቱን ለሸማች (ለተጠቃሚ) ያለምንም አድልዎ አገልግሎት ይሰጣል፤

2/ በሶስቱም የነዳጅ አይነቶች በቂ የነዳጅ ክምችት መያዝ የሚያስችል ማከማቻ ታንከር ያዘጋጃል፤

3/ መብራት ሲጠፋ አገልግሎቱን ማስቀጠል የሚያስችል አማራጭ ሃይል/ጄኔሬተር/ ያመቻቻል፤

4/ በታንከር ውስጥ ያለን የነዳጅ መጠን ለማወቅ ልኬታው በትክክል መነበብ የሚችል ዲፕስቲክ መሳሪያ፣ ማናበቢ ያዘጋጃል፤

5/ በሶስቱም የነዳጅ አይነቶች የነዳጅ ጥራትን መለየት የሚያስችሉ ሃይድሮ ሜትር መሳሪያያመቻቻል፤

6/ የሚሰራና በቂ የጋዝ መጠን ያለው የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ ያዘጋጃል፤

7/ በአገልግሎት አሰጣጥ አጭር ስልጠና የወሰዱና መልካም ስነ-ምግባር ያላቸው ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያሟላል፤

8/ ለነዳጅ ማደያ ሰራተኞች መለዮ ልብስ (ዩኒፎርም)፣ የደህንነት መጠበቂያ ጫማ (ሴፍቲሹዝ)፣ የእጅ ጓንት/ግላብ/፣ ,የዓይን መነፅር /safety goggle/ መለያ ቁጥር ያለው ባጅ ያሟላል፤

9/ ከተፈቀደላቸው ከነዳጅ ማደያ ሰራተኞች ውጭ በሌላ አካል ነዳጅ አለማስቀዳት፤

10/ በሕግ የተወሰኑ ጉዳዮችን የተመለከቱ መረጃዎች ማለትም የጸና ንግድ ፈቃድ፣ ወቅታዊ የዋጋ ተመን ዝርዝር፣ የንግድ ስም ታፔላ ተጠቃሚው ሊያየው በሚችል ቦታ ያስቀምጣል፤

11/ የተሸጡትን ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች እንዲሁም የተሸከርካሪ ቅባቶችን በመጠን፣ በዓይነትና በዋጋ ለይቶ በየወሩ ለንግድ ተቋም የጽሁፍ ሪፖርት ያቀርባል፤

12/ የነዳጅ ሽያጭን ሀጅና ቀሪ ባለው ህጋዊ ደረሰኝ በመጠቀም ለደንበኞች ህጋዊ ደረሰኝ ይሰጣል፣ ቀሪ ደረሰኙንም እስከ አስር አመት ድረስ አደራጅቶ ያስቀምጣል፤

13/ ሶስቱን አይነት የነዳጅ ታንከሮች ለየራሳቸው አገልግሎት ብቻ ያዉላል፤

14/ የነዳጅ ማሽኖች ሲበላሹ ከነዳጅ አቅራቢ ካምፓኒው ጋር በመነጋጋር በፍጥነት የጥገና ስራ ያስፈጽማል፤

15/ ተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት በቁጥጥርና በክትትል ወቅት ለድርጅቱ አስተያየት የሚሰጥበት የአስተያየት ደብተር ያዘጋጃል፣ የሚሰጠውንም አስተያየት ተግባራዊ ያደርጋል፤

16/ ሁሉንም የነዳጅ ማሽኖች በተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት በአመት አንድ ጊዜ የቬሪፊኬሽን ምርመራ ያስመረምራል፤

17/ በመመሪያው መሰረት ቬሪፋይ ተደርጎ በባለሙያዎች በፕሎምፕ የታሰረውን መደበኛ ቶሎራንስ (በ20ሊትር+/-100ml(+/-0.5%) ገደብ ይጠብቃል፣ ችግር ሲፈጠር ለተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት ያሳዉቃል፤

18/ ለነዳጅ አቅራቢ ካምፓኒው አስፈላጊውን የነዳጅ ክፍያ በወቅቱ ይከፍላል፣ ከነዳጅ አቅራቢ ካምፓኒው ጋር በገባው ውል መሰረት ተግባራትን ይፈጽማል፤

19/ የመኪና እጥበት የፍሳሽ መስመር፣ የተቀየረና የተቃጠለ ዘይት ማስወገጃ፣ የትራፊክ ፍሰት ጠቋሚ፣ የፍሳሽ ማድረቂያ ንፁህ አሸዋ፣ ኮምፕረሰር ያሟላል::

ክፍል አራት

ስለነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት

9. የነዳጅ አቅርቦትና ስርጭት አፈጻጸም

1/ በማንኛውም ቦታ የነዳጅ ችርቻሮ የሚፈጽም ግለሰብ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ ካልተያዘ እንዲሁም በመንግስት የችርቻሮ የመሸጫ ዋጋ ተመን ካልሸጠ በስተቀር ግብይቱን መፈጸም የተከለከለ ነው፤

2/ የነዳጅ ማደያ ባለበት ከተማ 15ኪሎ ሜትርራዲየስ ውስጥ ከነዳጅ ማደያዎች በስተቀር ሌላ ግለሰብም ሆነ ድርጅት የነዳጅ የችርቻሮ ፍቃድ አዉጥቶ መቸርቸር አይችልም፤

3/ ከዚህ አሰራር ውጭ የንግድ ስራ ፈቃድ የሰጠ ባለሙያ ወይም ቡድን መሪ ወይም ሃላፊ በዲስፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፤

4/ በ15 ኪ.ሜ ሬዲየስ ውስጥ ነዳጅ ማደያዎች በማደያው የነዳጅ መሸጫ ዋጋ ለማንኛውም ተጠቃሚ በማደያ መሸጫ ዋጋ የመሸጥ ግዴታ አለባቸው፤

5/ እያንዳንዱ ነዳጅ ማደያ ለቤንዚን 3000 ሊትር፣ ለናፍጣ 5000 ሊትር፣ ለኬሮሲን 1000 ሊትር ታንከሩ ውስጥ ሪዘርብ ሲቀረው ቀጣዩን ክምችት ከነዳጅ አስመጭ ኩባንያዎች የማስመጣት ግዴታ አለበት፤

6/ በነዳጅ ማደያው ታንከር ውስጥ የሚገኘው የነዳጅ መጠን በሪዘርብነት መቀመጥ ያለበት መጠን ከሆነ ያለ ወረዳው ወይም ከተማው ወይም ክ/ከተማው ንግድ ጽ/ቤት ትዕዛዝ የነዳጅ ማደያው ነዳጅ መሸጥ አይችልም፤

7/ እንዲህ አይነት የነዳጅ እጥረት ሲያጋጥምና ሪዘርቭ ሲገባ የንግድ ተቋም ብቻቅድሚያ ለሚሰጣቸው የመንግስትና አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ነዳጁ በኩፖን እንዲሰራጭ የማድረግ ስልጣን አለው፤

8/ የነዳጅ እጥረት በሚፈጠርበትና ሪዘርቭ ነዳጅ በሚያዝበት ወቅት ለፀጥታና ደህንነት ተግባራት (ፖሊስ፣መከላከያ)፣ ለማህበራዊ አገልግሎት (ጤና፣ ወፍጮ ቤቶች፣ መብራት፣ ቴሌ፣ ቀይመስቀል፣ እሳት አዳጋ፣ አምቡላንስ፣ ቱሪስት፣) ለግብርናና ኢንዱስትሪ ልማቶች መስኖ፣ ኢንዱስትሪና መሰረተ ልማት አገልግሎት፣ ለህዝብ ጭነትና ለፈሳሽ ጭነት አገልግሎት ወዘተ ቅድሚያ ተሰጥቶ በኩፖን ነዳጅ እንዲጠቀሙ ይደረጋል፤

9/ አዲስ የነዳጅ ማደያዎች ከመከፈታቸው በፊት የክልሉ ንግድቢሮ አስፈላጊነቱን በድጋፍ ደብዳቤ ካልፈቀደ በስተቀር የነዳጅ ማደያ ግንባታ ማካሄድ አይቻልም፤

10/ በገጠር መስኖ ልማት የተሰማሩ ጀኔሬተር የሚጠቀሙ አርሶአደሮች፣ የተደራጁ የመስኖ ህብረት ስራ ማህበራት፣ አልሚ ባለሀብት ከወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት ህጋዊ የድጋፍ ደብዳቤ ካላመጡ በስተቀር ነዳጅ ከማደያ መቅዳት አይችሉም፤ ሆኖም ህጋዊ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ከቻሉ በማደያ መሸጫ ዋጋ ነዳጅ የመግዛት መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

11/ ጀልባ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ጀልባዎች የሚጠቀሙትን ነዳጅ የጀልባ ባለቤት የሆነው ህጋዊ አካል በማደያ መሸጫ ዋጋ ከነዳጅ ማደያ መግዛት ይችላል፤

12/ ነዳጅ ማደያ ከሚገኝበት ከ15 ኪሎ ሜትርራዲየስ ውጭ ለሚገኙ ባጃጅ ተሸከርካሪወች የነዳጅና ቅባት ችርቻሮ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ ወይም ድርጅት በማደያ መሸጫ ዋጋ ነዳጅ የመግዛት መብቱየ ተጠበቀ ነው፤

13/ ሰሌዳ የሌላቸው ጀልባዎች፣ ባለ3 እግር ባጃጆች፣ ሞተር ብስክሌቶች፣ መኪናዎች ነዳጅ መግዛት አይችሉም፤

14/ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ የሌላቸው ጀልባዎችና ባለ ሶስት እግር ባጃጆች እንዲሁም የጭነት ተሽከርካሪዎች ነዳጅ መጠቀም አይችሉም፤

15/ ከ15 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውጭ ያሉ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው የቅባትና የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በበርሜልና በጀሪካን ነዳጅ መግዛት ይችላሉ፤

16/ የነዳጅ እጥረት ካጋጠመና በመደበኛው ስርጭት ማስፈጸም የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ቢሮው በሰርኩላር ደብዳቤ በሚያሳዉቀው መሰረት ላልተወሰነ ጊዜ የነዳጅ ስርጭቱ ሙሉ በሙሉ በኩፖን ብቻ እንዲሰራጭ ይወስናል፤

17/ ማንኛውም የእምነት ተቋም፤ የመንግስት የልማት ድርጅት ከተቋሙ በተፃፈ ህጋዊ ደብዳቤ ነዳጅ በማደያው የመሸጫ ዋጋ የመግዛት መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

18/ ከክልሉ ውጭ የሚመጡ የሌላ ክልል የነዳጅና ቅባት ችርቻሮ የጸና የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ቸርቻሪዎች በክልሉ በሚገኙ ነዳጅ ማደያወች ነዳጅ መግዛት አይችሉም፤

19/ በክልሉ የሚገኙ ከማደያ ውጭ የነዳጅና ቅባት የችርቻሮ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ቸርቻሪዎች አገልግሎት ከሚሰጡበት መስመር ውጭ ወደሌላ አካባቢ ነዳጅ ማንቀሳቀስ አይችሉም፤

20/ በክልሉ የሚገኙ ከማደያ ውጭ የነዳጅና ቅባት የችርቻሮ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ቸርቻሪዎች የጸና የንግድ ስራ ፈቃዳቸውን በማሳየት ከነዳጅ ማደያ በማደያው የመሸጫ ዋጋነዳጅ መግዛት ይችላሉ፤

21/ በክልሉ የሚገኙ ከማደያ ውጭ የነዳጅና ቅባት የችርቻሮ የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ቸርቻሪዎች ከመንግስት የመሸጫ ተመን በላይ ነዳጅ ሸጠው ከተገኙ አስተዳደራዊ ርምጃ ይወሰድባቸዋል፤

22/ በገጠር የሚገኙ ወፍጮ ቤቶች ህጋዊ ፍቃድ ከሌላቸው ወይም ፍቃዳቸው በዘመኑ የታደሰ ካልሆነ ወይም ከወረዳው የንግድ ሴክተር የድጋፍ ደብዳቤ ካላመጡ በስተቀር ነዳጅ ከማደያ መቅዳት አይችሉም፤ ሆኖም የጸና የንግድ ስራ ፍቃድ ወይም ህጋዊ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ከቻሉ በማደያ መሸጫ ዋጋ ነዳጅ የመግዛት መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

23/ የነዳጅ ማደያው ነዳጅ ከታንከሩ አውጥቶ በጀሪካን ወይም በበርሜል በመከዘን ለአካባቢው ህብረተሰብ በችርቻሮ ዋጋ መሸጥ አይችልም፤

24/ የነዳጅ ማደያው በ15 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ለሚገኙ ደንበኞች ከታንከሩ ውስጥ በማሽን እየቀዳ በነዳጅ ማደያው የነዳጅ መሸጫ ዋጋ የመሸጥ ግዴታ አለበት፤

25/ ዞኑ ከ15 ኪሎ ሜትር ራዲየስ ውጭ ለሆኑ ቦታዎች በዞኑ የገበያ አረጋጊ ግብረ ሃይል በማስወሰን የነዳጅ ችርቻሮ የንግድ ፍቃድ ለአካባቢው ሰው በመስጠት ነዳጅ ለአካባቢው ህብረተሰብ እንዲሰራጭ የማድረግ ሃላፊነት ይኖርበታል፤

26/ ነገር ግን የገጠር ወፍጮና መስኖ ልማት ያላቸው ግለሰቦችና ማህበራት ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ እስካመጡ ድረስ ከነዳጅ ማደያው በማደያው የመሸጫ ዋጋ የመግዛት መብታቸው የተጠበቀ ነው፤

27/ ከነዳጅ ማደያ 15 ኪሎ ሜትር ሬዲየስ ውጭ ሆኖ የችርቻሮ ፈቃድ አውጥተው በግብረ ሃይሉ ዋጋ ተመን ወጥቶላቸው ለሚሰሩ የነዳጅ ችርቻሮ ፈቃድ ላላቸው ቸርቻሪዎች የሚፈቀደውን የነዳጅ መጠን የወረዳው ወይም የከተማው ንግድ ተቋም ሊገድብ ይችላል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. የመተባበር ግዴታ

1/ ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2. ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ እንደየአግባቡ አስተዳደራዊ፣ ፍትሐብሄራዊና የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል።

11. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ማስፈጸሚያ መመርያ ቁጥር 02/2009 ስለ ነዳጅ ስርጭት የተደነገጉ አንቀጾች በዚህ መመርያ ሙሉ በሙሉ ተሸረዋል፤

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ተፈጻሚነት የላቸውም።

12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከሰኔ1/2010 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

አገኘሁ ተሻገር

የአብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ